| | |
|---|---|
| **ርእስ፡-** | **ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ** |
| የጽሑፍ ዓይነት ፡- | ግለ ታሪክ |
| ጸሐፊው (ደራሲው)፡- | ስዩም ወልዴ ራምሴ |
| የኅትመት ዘመን ፡- | 2002 |
| የገጽ ብዛት፡- | 360 |
| ዋጋ፡- | ብር 50.00 |
| የታተመበት ቦታ፡- | አዲስ አበባ |
| አሳታሚ፡- | የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርና አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ተሏሏሪ ሂሳብ አስተዳደር የታተመ |

በደረጀ ገብሬ[1]

## የግለ ታሪኩ ይዘት

‹‹ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ›› የአንድን ታዋቂ የሥነ ጥበብ ሰው ከልደት እስከ ሀምሳ ዓመት ድረስ ያለውን ውጣ ውረድ የሚተርክ፣ ግለ ታሪክ ነው፡፡ ጸሐፊው ‹‹እነሆኝ›› ብሎ በሰየመው የማስተዋወቂያ ቀዳሚ ክፍል፣

> በጽሑፌ ውስጥ ያተኮርኩት እኔ ሌሎችን እንደማያቸውና እንደማውቃቸው እንጂ እንደሚያዩኝና እንደሚያውቁኝ አይደለም፡፡ አንባቢዬ እዚህ ህሊና ክርክር ውስጥ አይግባ- የምነግረው እውነቴን እንጂ ሀቁን አይደለም፤ ስለዚህ ነው እንዳየሁት ብዩ የምናገረው፡፡ ... ሰዎች

---

1 በቋንቋዎች ጥናት ፋከልቲ የአማርኛ ክፍለ ትምህርት መምህር

የተናገሩኝን እንጂ ያሰቡኝን ማወቅ አልችልም፤ ያደረጉትን እንጂ ሊያደርጉ የፈለጉትን ማለት አልችልም። (ገጽ 10)

ሲል እንደጠቆመው በግል ልምዱና አመለካከቱ ላይ ተመርኩዞ ያጋጠመውንና የኖረውን፣ ልዩ ልዩ የሕጻንነት፣ የልጅነት፣ የትምህርትና የሥልጠና እንዲሁም የሥራ ኃላፊነት ያስከተሉበትን ትሩፋትና ፍዳ ከግል አቋሙ አንፃር ቁልጭ አድርጎ በማያሻማ ቋንቋ አቅርቦልናል። የግለ ታሪኩን መሠረታዊ ማጠንጠኛና ጠቀሜታ ከሚከተሉት ነጥቦች ማስተዋል ይቻላል።

- ‹‹ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ›› ግለታሪክ በ360 ገጾች ውስጥ የተካተተ ትረካና 23 ያህል ፎቶዎችና ሥእሎች የሚገኙበት ድጉስ ነው። የሽፋን ፎቶው የባለታሪኩን እውናዊ ገጽታ የሚያሳይ ከመጽሐፉም አጠቃላይ ይዞታ ጋር ተዛማጅነትና ሕያውነት ያለው ሆኖ ይታያል።
- በግለ ታሪኩ አማካይነት በዘመኑ ስለነበረው የአዲስ አበባ የልጆች አስተዳደግ፣ በተለይም በተርታው ቤተሰብ ውስጥ ያለው የልጆች አያያዝ እምብዛም ከገጠሩ ያልተለየ መሆኑን ያሳየናል። ትምህርትን ከቄስ ትምህርት ቤት መጀመር፣ የየኔታን እግር መሳም፣ ኩርኩም፣ ቁንጥጫ፣ በባዶ እግር መሄድና በምስማር መወጋት፣ ወፎችን በድንጋይ መምታት፣ ዛፍ ላይ መውጣት፣ በአካባቢ የሚገኝ ሙክት ላይ መቀመጥና ጥርስን መሰበር፣ አህያም ሆነ ፈረስ ካጋጠመ ተቀምጦ ለመጋለብ መጣጣር፣ በተገኘው ነገር ሁሉ መሳተፍና የሚያጋጥመውን በጥሞና መቀበል ሁሉ በልጅነት የሚያጋጥሙ ተደጋጋሚ ድርጊቶች ናቸው፤ የከተሜው ስዩምም የልጅነት ሕይወት ይኸው ነው። ከእናት

ቁንጥጫና ግርፊያ፣ ከበርበሬና ከኮሶ መታጠን ጋር የተያያዘ ቅጣት ልማዳዊ ከልጅ ገርቶ ማሳደጊያ ብልሃቶች አንዱ እንደነበር የሚመሰክር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ያልኩትን ይበልጥ ለመረዳት ግን፣ ‹‹ደማቁ ጠዋት›› የሚለውን የመጀመሪያውን ምእራፍ ስታነብቡ አሁን ከተቀስኩላችሁ ይበልጥ አስቂኝ፣ አስገራሚና አሳሳቢ አንዳንድ ጊዜም አሳዛኝ ትረካዎች ታገኛላችሁ፡፡

- የከተማው አስተዳደርና እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪ በምን ዓይነት አቅድ (ፐላን) በተሠሩ ቤቶች ውስጥ ይኖሩ እንደነበር፣ ዛሬ የምናያቸውና በልዩ ልዩ ሰበብ እየፈረሱ የምናስተውላቸው የከተማዋ ቤቶች አጀማመራቸውና አመሠራረታቸው እንዴት እንደነበረ፣ የመንገዶችና ጎዳናዎች አሠራርና አካሄድ፣ የራዲዮ መርሀ ግብር ስርጭት፣ በተለይም የዘፈን መርሀ ግብር ሲኖር ዘፋኞች ከነሙሉ መሳሪያቸውና አጀባቸው ራዲዮ ጣቢያው ድረስ እየሄዱ ያቀርቡ እንደነበር (ዛሬ ሕያው የምለው ዓይነት አቀራረብ) የልጅነት ገጠመኙን አንተርሶ ይተርክልናል፤ በዚያም የተነሳ የአዲስ አበባ የሕይወት ምህዋር  እንዴት እንደሚሽከረከር በማሳየት ረገድ ይህ ግለ ታሪክ የበኩሉን ጭላንጭል ያሳያል፡፡ በዚህም ምክንያት ግለሰቡ በኖረበት ዘመን ላይ በአዲስ አበባ አስተዳደርና በነዋሪዎቹ ማኀበረ ባህላዊ ግንኙነትና ሕይወት ላይ ጥናት ለሚያካሂድ ተመራማሪ የጊዜውን ወረራ (መልክ) ለመመልከት ያስችለዋል፡፡
- በዚህ ግለ ታሪክ ውስጥ በቀጥታ ከማይነገሩ ነገር ግን እንደገጠመኝ ከሚፈነጠቁ ቁም ነገሮች ውስጥ በነስዩም መኖሪያ ሰፈር በነበረው የሳት

አደጋ ግቢ ውስጥ ተጥሎ የተገኘው የብረት ሐውልት ጉዳይ ነው። ስዩም ያንን ሀውልት በድንጋይ ሲቀጠቅጠው በሚሰጠው ድምጽ ይደሰታል። በዚህ ብቻ ግን አያበቃም። ገጽ 25 ላይ ማንበብ ያቻላል።

- በአዲስ አበባ ከተማ ስለነበረው የትምህርት አሰጣጥና የመምህራን ድርሻ፣ ከዜግነት ስብጥርና ከሥልጠና ብቃትና እምነት ጋር ለመተዋወቅ የሚበጁ ጥቆማዎች ያቀርባል። ስለመምህራኑ ትጋት፣ ስለትምህርት ቤቶች ስርጭት፣ ንጉሠ ነገሥቱ በትምህርት ቤቶች፣ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በወላጆች ላይ ስለነበራቸው ተጽእኖ (ምንም እንኳዋን በተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ሁኔታና ቦታ በተደጋጋሚ የተገለጸ ቢሆንም) የዓይን ምሥክር ሆኖ የሚቀርብ ነው። ለምሳሌ ከክፍል አንደኛ ለሚወጣ ተማሪ፣ ወይም ከሚማራቸው ትምህርቶች ውስጥ ብልጫ ሲያመጣ የዚያ ትምህርት መምህር በግሉ ስለሚሰጠው ማበረታቻና ሽልማት ሁሉ ስናነብ በአሁኑ ጊዜ በሥራው ላይ የምንገኝ መምህራን ወደ ውስጣችን እንድንመለከት አንዳች የመንፈስ ግዴታ ሽው እንዲልብን የሚያደርግ ይመስለኛል።
- በዘመኑ ስለነበረው የሥራ አቅርቦትና የወጣቶች ተጠቃሚነት አንዳች መረጃ ለሚሻ የበኩሉን ድርሻ ይፈነጥቃል። በገጠርም ይሁን በከተማ ተወልደው የሚያድጉ ሕፃናት እድሜያቸው በደረሰበት ደረጃ ቤተሰቦቻቸውን በሥራ ያግዛሉ፤ በልዩ ልዩ ገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ ለግል መጠቀሚያ የሚሆናቸውን ገንዘብ ለማግኘት ይተጋሉ፤ ወጣቱ ስዩም ወልዴም በዚህ ዓይነት ተግባር ይሳተፍ እንደነበረ፣

ከትምህርት ቤት ውጪ ባሉ ትርፍ ጊዜዎቹ ከጓደኞቹ ጋር ከመጫወት አልፎ በንግድ፣ በእጅ ሥራ ሽያጭ፣ በሥእል ሥራና በልብስ ስፌት ጭምር ራሱን ጠምዶ ለትምህርት ቤት የሚሆኑትን ቁሳቁሶች ለማሙዋላት ጥረት ያደርግ ነበር፤ አልፎ ተርፎም ለእናቱ የዘመን መለወጫ በግ ሳይቀር ለመግዛትና ለማሳረድ መቻሉን በደስታ እንደሚያስታውሰው እናነባለን፡፡ ቀላልና አብዛኛው የዚያ ዘመን ወጣቶች ይፈጽሙት የነበረ ተግባር ሊሆን ወይም ሊመስል ይችላል፡፡ ጉዳዩ እሱ አይመስለኝም፡፡ አሁን ላለንበት ኅብረተሰብ በተለይም ለወጣቱ ክፍል የሚኖረው ምሳሌነት ነው፡፡ እርግጥ አሁንም የሥራ ስምሪቱና ዓይነቱ ይለያይ ይሆናል እንጂ በየአካባቢያችን በናሙናነት የምናነሳቸው ሊስትሮዎች፣ ቆሎ ሻጮች፣ ሳምቡሳና ብስኩት አዙዋሪዎች፣ እንዲሁም የቅርብ ክስተት ይሁን እንጂ የመጻሕፍት ሱቅ በደረቴዎች፣ ሎተሪ ሻጮች፣ ተሸካሚዎች ልጆች አናጣ ይሆናል፡፡ የስዩም ትረካ ግን ተግባሩ ከግማሽ ምእተ ዓመትም በፊት የነበረና የብዙ ወጣቶችና ቤተሰቦች ተፈታታኝ እውነታ እንደነበረ ያሳየናልና እንማርበታለን፡፡ የወደፊቱም አንባቢ ይበልጥ ይገለገልበታል ብዬ እገምታለሁ፡፡

- እንዲሁም ባለ ግለ ታሪኩ በነበረው ግላዊ ትጋትና ብርታት፣ ከግለሰቦችም ባገኘው ድጋፍ የሥዕል ኤግዚቢሽን ለማሳየትና በታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጭምር ለማስጎብኘት ችሏል፡፡ ከዚያም ተነስቶም የወደፊት ሕይወቱን መቀየስ እንደቻለ አመላክቶአል፡፡ በመሆኑም አንባቢ፣ በተለይም ወጣቶች ብዙ ምሳሌነት ያለው ቁም ነገር

ሊቀስሙበት ይችላሉ፡፡ በኃላፊነት ላይ የምንገኝ ወገኖችም ወጣቶቻችንን መምከርና ማበረታታት የሚያስገኘውን ታላቅ ጠቀሜታ እንቀስምበታለን ብዬ አምናለሁ፡፡

- በወጣትነት ዘመኑ በተሳተፈበት የጋዜጠኝነት ሙያም በኩል ያጋጠሙትን ልዩ ልዩ ውጣ ውረዶች ሲገልጽ እግረ መንገዱን የዘመኑን ሀሳብን የመግለጽ እውነታ ከነተግዳሮቱ ያሳዬናል፡፡
- የሙያ ወይም የነፍስ ጥሪ አድርጎ በመረጠውና በሥነ ጥበብ ምርምር ላይ ከፍተኛ ሥልጠና ለማግኘት በነበረው ፍላጎትና ትጋት ወደ ሶቪየት ኅብረት ሄዶ ትምህርቱን መከታተሉን የመጽሐፉ ሢሶ ያህሉ ገጾች ያስረዱናል፡፡ በዚያ የትምህርት ዘመንም ያሳለፈውን ሕይወት በሚገልጽባቸው ገጾች ሁሉ የሚያቀርባቸው ልምዶች፣ ምንም እንኳን የግለሰብ መስለው ቢታዩም፣ በዘመኑ የውጪ አገር ትምህርት አያያዝ ላይ ጥቂት ብርሃን መፈንጠቃቸው አይቀርም፡፡ የ‹‹መንገዳማውን ረፋድ›› ረጅም ምዕራፍ በጥሞና ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ ስዩም ወደ ሶቪየት ኅብረት ሄዶ እስከተመለሰበት እለት ድረስ ያለውን ውጣውረድ ፍንትው አድርጎ ያሳየበት ምንባብ እንደሆነ ታዩታላችሁ፡፡ በተለይ አገራችን በለውጥ ማእበል ከመናጧ አስቀድሞ ወደ ሩሲያ ሄደው የመማር እድል ከገጠማቸው ውስጥ የፊታውራሪ ተክለሐዋሪያትን ‹‹የሕይወቴ ታሪክ›› ያነበበም ሆነ ይህንን የስዩምን ‹‹ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ›› የሚያነብ ወገን በተለምዶ ከአብዮት በፊት በምንለው ዘመን ሩሲያውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የነበራቸውን የላቀ ግምት

ሲረዳ እጅግ አድርጎ መደነቁ አይቀርም፡፡ ስዩም ከገጽ 172- 174 ባሉት ትረካዎቹ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የቤት እንሰሳትን በተለይም የውሻን አያያዝ ተገን አድርጎ የሚተርክልን ገጠመኝ እንዲሁ ፈገግም ተከዝም የሚያስደርግ ይዘት አለው፡፡ በድምሩ ስዩምን ያጋጠሙት አብዛኞቹ ሩሲያውያን በእምነታቸው እናንተ ኢትዮጵያውያን ‹‹ልዑላን ናችሁ›› እስከማለት የሚደርስ ሰብአዊ ሚዛን እንደነበራቸው እናነባለን፡፡ በጠቅላላው ስለአፍሪካውያንም ሆነ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ዓይነትና ስብጥር በወጉ ተርኮልናል ማለት ይቻላል- በ‹‹እነሆኝ›› ላይ በጠቆመን መሠረት ስንመለከተው፡፡

- በጥቅሉም ሲታሰብ፣ ውጪ አገር ሄደው የሚማሩ ተማሪዎች የሚያጋጥሙዋቸውን የአካባቢና የባህል ግጭት ሁሉ በምሳሌ እያጣቀሱ ስለሚያሳዩን አንዳች የመደነቅና የመገረም ስሜት ያድርብናል፤ እርካታም አናጣበትም፡፡ ቡልጋሪያ ሄዶ በአንድ ሆቴል ውስጥ ምግብ ለማዘዝ ያየውን ፍዳና ያጋጠመውን ከበግ ጭንቅላት ጋር ያደረገውን ፍጥጫ ስናነብ ተራኪነቱንም ሰዓሊነቱንም አጣምሮ የያዘ ባለሙያ እንደነበረ ለመመስከር እንገደዳለን፡፡
- በተጨማሪም በልዩ ልዩ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ጥበባዊ ጉባኤዎች ላይ በአዘጋጅነት፣ በተባባሪነት፣ በጥናት አቅራቢነት የተሳተፈ በመሆኑ በነዚያ መድረኮች ሁሉ ያገራችንን ኪነ ጥበብ በማስተዋወቅ ረገድ ያደረገውን ጥረት፣ በወቅቱ ስለነበረው ዓለማቀፋዊ የአስተሳሰብና የትኩረት ምርጫ ሁሉ በግልጽ ያቀርብልናል፡፡ በዚያም ሰበብ ታሪካዊ

ዋጋ ያላቸውን መረጃዎች እንቃርማለን፡፡ ሌሎችንም በርካታ የይዘት ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ የራሱን አገር የኢነጥበብ እድገትና ደረጃ በመመዘን ጎደሎው ጎናችን እጅጉን አመዝኖ ያየውና ሲብከነከን እናስተውላለን፡፡ እንዲሁም ወደ ብቃት የማሳደግ ልፋት ተገቢነት ፍንትው ብሎ ይታየውና ወደፊት ለማስኬድ ሲጣጣር ከሚገጥሙት ፈተናዎችና ጣጣዎች ጋር አዋህዶ ያቀርብልናል፡፡

- በሌላም አቅጣጫ፣ በወቅቱ ከየትኛውም አገር ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ አገራቸው ይመለሱ የነበሩ ተማሪዎች ወገናቸውን ለማገልገል የነበራቸውን የመንፈስ ዝግጅት ከአቶ ስዩም ወልዴ ግለ ታሪክ ፍንጭ እናገኛለን፡፡ አቶ ስዩም በፊት ወደ ውጪ ሀገር ለትምህርት የሚሄዱ ወገኖች ፍላጎትና ስሜት ምን እንደነበረ ከአንዳንድ ግለሰቦች ታሪክ ስንሰማው የኖርነው ነው፡፡ ከላይ እንደጠቆምኩት፣ ባለ ታሪኩ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ አገሩ የተመለሰበት ወቅት በአገራችን ሥር ነቀል የሆነ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ የተደረገበት ነበር፤ ያንን ለውጥ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ከነውጣ ውረዱ፣ ከነዝባዝንኬው፣ ከነትርምሱ፣ ከነምስቅልቅሉ አቅርቦልናል፡፡ በዘመነ አብዮት መጀመሪያ አካባቢ አገሪቱን አናውጧት ስለነበረው ቀይና ነጭ ሽብር እንዲሁ የሰማውንም ሆነ ያየውን ስቃይና ሰቆቃ ስእላዊ በሆነ መንገድ ፍንትው አድርጎ ያሳዩናል፡፡ ይህንኑም ገለጻውን ‹‹ያልጠረረ ቀትር›› በሚለው ሦስተኛው ምዕራፍ ላይ በሚገባ ገልጾታል፡፡ ስለዚያ

አሰቃቂ ዘመን የወ/ሮ ቆንጂትን ምርኮኛ የተሰኘ ልቦለድ ማንበብም የስዩምን ትዝብትና ልምድ ይበልጥ ለመረዳት ያስችላል፡፡

- አንድ ሰው በተሰለፈበት ሙያም ሆነ በሚመደብበት ኃላፊነት ይበልጥም ደግሞ በኮሚቴ ሥራ ውስጥ ተግቶ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለሚመጡ የኮሚቴ ሥራዎች ሁሉ እየታጨና እየታዘዘ መካራ ስቃዩን ያይ እንደነበረ ይህ ግለ ታሪክ ዓይነተኛ ምስክር ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በየሺጥላ ኮከብ የተደረሰው ‹‹ዶሰኛው›› የተሰኘ መጽሐፍ በልቦለድ መልክ ያቀረበውን አንድ ሰው በ13 ኮሚቴ ውስጥ እንዲሳተፍ የተደረገበትን ትረካ እና በግለሰቦች ላይ ይፈጥር የነበረውን የኀሊና ትርምስ እንዲታወስ ያደርጋል፡፡

## የአጻጻፍ ገጽታ

ከላይ እጅግ በጣብ ቁጥብ በሆኑ ነጥቦች በስዩም ግለ ታሪክ ውስጥ ከተገነዘብኳቸው ውስጥ ጥቂቶቹን ለመግለጽ ሞክሬያለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ስለአገላለጽ ኃይሉ ጥቂት ነጥቦች ላንሳ፡፡ እርግጥ ስዩም ከሕይወት ታሪኩና ከሌሎቹ ሥራዎቹ አኩዋያ ሲታይ የሥነ ጥበብ ታሪክ ተመራማሪና ሃያሲ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይሁንና ይበልጥ የሚታወቀው ግን በሰዓሊነቱና በስዕል ጥበብ መምህርነቱ እንደሆነም አውቃለሁ፡፡ ይሁንና በሥዕል ረገድ ያለው ተሰጥኦ ምን ያህል እንደሆነ በእኔ ሊመዘን ቀርቶ ሊታሰብ አይችልም፡፡ ቀረበም ራቀ የጥበብ ዋነኛ ገጽታና ጠቀሜታ

ሕይወትን ከነውስጣዊ ውስብስብም ሆነ ቅንጭብጭብ ዘርፉዋ ማሳየት እንደሆነ አምናለሁ። ፍርዱ የተመልካችም እንደሆነ ሁሉ እገነዘባለሁ።

በዚህ ግለ ታሪክ ግን፣ በተለይ በቋንቋ አጠቃቀሙ በኩል፣ ጥቂት ምሳሌዎችን በማንሳት ማሳየት ይገባል።

ስዩም ሀሳቡን ወደ አንባቢ የሚያደርስባቸው የቃላት ምርጫዎቹና የአረፍተ ነገር ቅንብሮቹ እጅግ ግልጽ ናቸው። በየትኛውም ገጽ ላይ ገልጣችሁ ብታነብቡ ለመረዳት የሚያስቸግር አገላለጽ ታገኛላችሁ ብዬ አልሰጋም። ቃላቱ ምስል ከሳች፣ አረፍተ ነገሮቹ ነጠላ፣ ወይም እጅግም ድርብርብነት (ውስብስብነት) የማይታይባቸው ናቸው። ለምሳሌ የአጼ ቴዎድሮስን ምስል ከመሥራቱ ጋር የተያያዘ ትዝብቱን ሲገልጽ፣

> ሠዓሊ አለ ፈለገ ሠላም የሐውልቱን ምስል ጥናት እንዲያቀርቡ ተደርጎ በየጊዜው የማሻሻያ ሀሳብ ሲሰጣቸው ቆይቶ የመጨረሻውን ጥናታቸውን አቅርበው ሐውልቱም ሳይሠራ ለውጥ ተካሄደ። ለውጡም ቴዎድሮስን ሲያመሰግን ሐውልቱን ሳያቆምላቸው አደባባዩ እስከ ዛሬ ባዶውን አለ። (ገጸ 113)

ሌላ ምሳሌ ለመጨመር፣ ሶቪየት ኅብረት በትምህርት ላይ ሳለ ስላጋጠሙት አንድ መምህር ሲገልጽ በሚከተለው አኳኋን ነበር።

> እስከነ መልካቸው አስፈሪ ናቸው። ግራጫ ጸጉራቸው ሁል ጊዜ እንደቆመ ነው። የፊታቸው ቆዳ ደም ያለው አካል አይመስልም- የገረጣ ነጭ ነው። ዓይናቸው ጎድጓዳ፣ የተንቀለቀለ፣ ጥርሳቸው

> የዘረዘረና በፓፒተስ ሲጃራ የበለዘ፣ ድምጻቸው የሻከረና በግፊት የሚወጣ ሰብአዊነት ያጣ ይመስላል፡፡ (ገጽ 183)
>
> ደስታ ታደሰ በጣም ከወደድኳቸውና ካከበርኳቸው በሕይወቴ ካጋጠሙኝ ኢትዮጵያውያን አንዱ ነበር፡፡ ... ሁሉን ሰው በእኩል የማየት፣ የማክበርና የመንከባከብ ባህርይ ያሳያል፡፡ ... ጸጉሩ በተፈጥሮው ቶሎ የሚያድግ ይሆንም በልማድ በአጭር የሚስተካከለው፣ ዐይኖቹ ፈጠጥ ፈጠጥ ያሉ አነስ ብላ በምትታይ ጭንቅላቱ ላይ ሰልካካነቱ የጎላ አፍንጫ ነበረው፡፡ ... (ገጽ 232)

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ገለጻዎችን ታገኛላችሁ፡፡ ስዩም ሲገልጽም ሆነ ሲተርክ ወይም ሲያስረዳ አለበለዚያም ተፎካካሪ ሀሳቦችን በክርክራዊ መንገድ ሲያቀርብ ቋንቋም ሆነ ያቀራረብ መንገድ ወይም ስልት የማይቸግረው ነበረ ማለት ይቻላል፡፡

## ማጠቃለያ አስተያየት

ከላይ የግለ ታሪኩን አጠቃላይ ትኩረት ጠቁሜያለሁ፡፡ ስለአገላለጽ ብቃቱም በተለይ መጠነኛ ምሳሌዎችን በማቅረብ ለማሳየት ጥሬያለሁ፡፡ ከነዚህ ላይ በመነሳት፣ ጽሑፉ በመታተሙ በአገራችን ዘመናዊ ሥነ ጥበብ ላይ ምርምር ለሚያካሂዱ መምህራንና ተመራማሪዎች፣ የታሪክ ተማሪዎች፣ ጽሑፉ ባተኮረባቸው ዘመናት

ውስጥ የነበረውን ያገራችንን ማኅበረ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለሚያጠኑ የሥነ ማኅበረሰብ ተመራማሪዎች ሁሉ እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እንዲሁም በኪነ ጥበብ ሙያ ውስጥ የየበኩላቸውን ድርሻ ለተወጡ ወገኖች ተገቢውን አክብሮት ከመስጠትና የታሪክ መታሰቢያዎችን ከማቆም አንጻር የማይናቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በአተራረክ ቅንብሩ፣ በቋንቋው ግልጽነት፣ ሥእላዊነትና ተስፋ ፈንጣቂነት ሰበብ ሕይወት ምንም ያህል ተግዳሮት ቢበዛባት በቆራጥነት ለሚጋፈጡዋት ወገኖች የራሱዋ ጣእም እንዳላት እንገነዘብበታለን፡፡ ራስን ለችግር ከማስገዛት ይልቅ ችግርን ለመግዛት መጣር ምንኛ አርኪ መሆኑን እናጣጥምበታለን ብዬ በግሌ አምናለሁ፡፡

በመሆኑም፣ ጠቅላላ አንባቢዎችም ከዚህ መጽሐፍ ብዙ ቁም ነገርም ሆነ የመንፈስ እርካታ ያገኙበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ከአለቆቻቸውና ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር የሚያደርጉዋቸው ክርክሮችና ግፍጫዎች ‹‹እኔ›› እያሉ መተረክ የሚፈጥረው ውስጣዊ ለራስ የማድላት ስጋት ‹‹እውነት ይሆኑ ይሆን?›› የሚያሰኙ ትረካዎች ቢመስሉም ኃላፊነትን ተቀብሎ መኖር እንዴት ዓይነት የአካልና የኅሊና ፈተና እንዳለበት የሚያስገነዝቡ በመሆናቸው ለወቅቱ አንባቢ የሥነ ልቦና ስንቅ ይሆናሉ ብዬም እገምታለሁ፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ አንባቢዎች የስዩምን ግለ ታሪክ አንብበው ሲጨርሱ ምናልባት በኅሊናቸው ውስጥ የሚብሰለሰሉ አንዳንድ ሰብአዊ ጥያቄዎች ማሰላሰላቸው አይቀርም፤ ከነሱ ውስጥ አንዱ ነጥብ ስዩም ወጣትነቱን እንዳለ በትምህርት፣

በሥራና በጉብኝት ክንዋኔዎች የማሳለፉን ያህል ለምን የወጣትነትን አንድ ገጽታ ማሳያ የሆነውን የማፍቀርና የመፈቀርን ጭብጥ ዘለለው የሚያሰኘው ነው፡፡ በአገር ውስጥ በትምህርት ቤት፣ በሥራም ዓለም በጋዜጠኝነት ከወዲያ ወዲህ ሲዘዋወርና ብዙ አድናቂዎች ሲያተርፍና በብዙዎች ዓይን መግባቱን የመግለጹን ያህል በኮረዶች ዘንድ ምንም ዓይነት የመፈለግ አዝማሚያ አላጋጠመውም? የእሱንም ዓይን የሳበች ወጣት አልነበረችም? እንዲሁም ውጪ አገር ሲማር እንዲህ ካለው ሰብአዊ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ታቅቦና የባህታዊ ኑሮ ነው ገፍቶ የመጣው?

ያም ሆነ ይህ ‹‹ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ›› ተነባቢና ጠቃሚም፣ ጠቋሚም መጽሐፍ ነው ብዬ እመሰክራለሁ፡፡